# ከምርጫ ቦርድ ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ /መድረክ/

<u>አዲስ አበባ፣</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ግንቦት 24 ቀን 2002 ዓ.ም. በቁጥር መድረክ 304/2002 ለቦርዱ ጽሕፈት ቤት ባቀረባችሁት አቤቱታ ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም. በመላው ሀገሪቱ የተካሄደው ጠቅላላ ምርጫ ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌዎችን፣ የምርጫ ሕግንና የምርጫ ስነምግባር ደንብን በጣሰ ሁኔታ ተከናውኗል በማለት ለማሳየት ከተፈፀሙት ሕገወጥ ተግባራት ከብዙው በጥቂቱ ያላችሁትን ዘርዝራችሁ ማቅረባችሁና ለዚህም ያስረዳልናል ያላችሁትን 87 ገፅ ማስረጃ አያይዛችሁ ማቅረባችሁ ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሠረት የአቤቱታችሁን ዝርዝር ቦርዱ ግንቦት 27 ቀን 2002 ዓ.ም. ባካሄደው 146ኛ አስቸኳይ ስብሰባው በስፋትና በጥልቀት መርምሮታል፡፡ በዚሁም በአቤቱታችሁ ዝርዝር፤

**በተራ ቁጥር** 1. የመራጮች ምዝገባ ሂደት ለኢ.ሕአዴግ ወገንተኛ በሆነ አኳኋን የተከናወነ ነው ብላችኋል፡፡

ቦርዱ የምርጫ አፈፃፀም የጊዜ ሠሌዳውን ረቂቅ በሕጉ መሠረት ቀደም ብሎ በምርጫው ለሚወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውይይት አቅርቧል፡፡ በዚህም ፓርቲዎቹ በተደረገው ውይይት እና የ5 ቀን ጊዜ ተሰጥቷቸው በጊዜ ሠሌዳው ላይ ያላቸውን አስተያየት በጽሑፍ ጭምር አቅርበዋል፡፡ በዚሁ የፓርቲዎች የጋራ አስተያየትና ስምምነት መሠረት ምርጫው ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም. እንዲካሄድና የመራጮችና የዕጩዎች ምዝገባ በጊዜ ሠሌዳው በተጠቀሱት ቀናት እንዲከናወን ተደርጓል፡፡

ቦርዱ በጊዜ ሠሌዳው የተጠቀሱት የዕጩዎችና የመራጮች ምዝገባ ጊዜ ተጣቧል ተጨማሪ ጊዜ ያስፈልገናል በሚል መድረክን ጨምሮ ሌሎቹም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያቀረቡትን ጥያቄ ተቀብሎ የተመቻቸ የውድድር ሜዳ ለመፍጠር ሲባል በመጀመሪያ የ10 ቀን በመቀጠልም የ20 ቀን ጊዜ በጠቅላላው ለዕጩዎች ምዝገባ የ30 ቀን ጊዜ አራዝሞ ምዝገባው ተካሂዷል፡፡

ከዚህም በላይ ደግሞ ለመራጮች ምዝገባ በመጀመሪያ የ10 ቀናት በመቀጠልም 5 ቀናት ተጨማሪ ጊዜ በመስጠት በአጠቃላይ ለ45 ቀናት እንዲከናወን አድርጓል፡፡

የመራጮች ምዝገባ ሂደት ለየትኛውም ፓርቲ ወገንተኝነት ባልታየበትና መራጩ ሕዝብ በየአካባቢው ለመመዝገብ አመቺ የሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች ተቋቁመውለት ከመቼው ጊዜ በላቀ መልኩ 32 ሚሊየን መራጮች የተመዘገቡበት እንደሆነ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም የገዢው ፓርቲ ደጋፊዎች እየተለዩ የሚመዘገቡበት አሠራር ፈፅሞ ባልነበረበት ሁኔታ በእናንተ በኩል በምን መልኩ ለኢ.ሕአዴግ ወገንተኛ በሆነ አኳኋን የተከናወነ መሆኑንን የሚያሳይ ተጨባጭ ማስረጃ እንዳላቀረባችሁ ቦርዱ አረጋግጧል፡፡

ይህንኑ ጉዳይም ተፈፅሟል በተባለበት ቦታ በምርጫ ሕጉ በተቀመጠው ሥነሥርዓት መሠረት አቅርባችሁ ስለማስወሰናችሁ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡

ስለሆነም ይህ ክስ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ቦርዱ በአንድ ድምፅ ወስኗል፡፡

**በተራ ቁጥር** 2. የዕጩዎች ምዝገባን ሂደት አወዛጋቢና ለኢ.ሕአዴግ ወገንተኛ በሆነ መልኩ የተከናወነ መሆኑን ገልፃችኋል፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር 1 ላቀረባችሁት ክስ በተብራራው መሠረት ተጨማሪ የዕጩዎች ምዝገባ ጊዜ ሲሰጥ ሁሉም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተለይም መድረክ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ዕጩ በማስመዝገብ ተጠቃሚ መሆናችሁን ቦርዱ በተጨባጭ አረጋግጧል፡፡

በተለያየ ምክንያት በለቀቁ ዕጩዎች ምትክም ቢሆን ለማስመዝገብ ለተወዳዳሪ ፓርቲዎች ተጨማሪ ዕድል ቦርዱ ሲሰጥ ከየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በተሻለ መልኩ መድረክ የዕድሉ ተጠቃሚ እንደሆነና ከ109 በላይ ዕጩዎችን ለማስመዝገብ እንደቻለ በተጨባጭ ያሉን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ቢሯችን ድረስ መጥታችሁ በመድረኩ ዋና ፀሐፊ በአቶ ጥላሁን እንደሻው አማካይነት ምስጋና እንደቸራችሁን የሚታወስ ነው፡፡

ይህ ደግሞ ቦርዱ ሁሉንም የፖለቲካ ፓርቲዎች ከሚገባው በላይ ሄዶ በእኩልነት ለማስተናገድ እና ለውድድር ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ብዙ እንደሰራ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ስለሆነም ያቀረባችሁት ክስ በማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ቦርዱ አልተቀበለውም፡፡

**በተራ ቁጥር** 3. በዚሁ ተራ ቁጥር ተፈፅሟል ያላችሁት ሕገወጥ ተግባር ስለመፈፀሙ በስፋት ያስረዳልናል ብላችሁ ያቀረባችሁት ማስረጃ የተጠቀሰውን ሕገወጥ ተግባር በስፋት ሁሉም የምርጫ ክልል ላይ ስለመፈፀሙ የሚያስረዳ አለመሆኑን ቦርዱ አጋግጧል፡፡

በዚህም በአባሪ 1 የቅስቀሳ ጊዜ በሰዓት ተገልፆ የተፃፈላችሁ ደብዳቤ በወቅቱ በነበረው አንዳንድ ህገወጥ የቅስቀሳ አካሄድ ችግሮች እንዳይከሰቱ በአንድ ወገን ላይ የተደረገ ክልከላ ሳይሆን በምሽት ወቅት በሚደረግ ቅስቀሳ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለማስቀረት በሚል ታስቦ የተፃፈ ነበር፡፡ ይህም አንዱን ፓርቲ ለመጉዳትና አንዱን ለመጥቀም ያለመ አለመሆኑን እና በሁሉም ፓርቲዎች ላይ የተሰጠ ውሣኔ መሆኑን ከደብዳቤው ይዘትና በወቅቱ በስፍራው ከነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ቦርዱ ለመረዳት ችሏል፡፡

ይህንኑ የበለጠ የሚያረጋግጠው ጉዳዩ ለቦርዱ ዋና ጽሕፈት ቤት ሪፖርት ከተደረገ በኋላ ለክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በአስቸኳይ የእርምት እርምጃና ድርጊቱን በፈፀመው ኃላፊ ላይ አስፈላጊው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

በጽሕፈት ቤቱ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በአድራሻው ለወረዳው የመድረክ ጽሕፈት ቤት በፃፈው እና በግልባጭ ለቦርዱ ጽሕፈት ቤት ባሳወቀበት ደብዳቤ ውሣኔው በእናንተ በኩል በበጎ ጎን አለመታየቱን ገልፆ በአፈፃፀም ረገድ የተሻረ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

በማከታተልም ድርጊቱን ለፈፀመው የምርጫ ክልሉ ኃላፊ የክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በደብዳቤ ከባድ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶታል፡፡

በአባሪ 2 የተፃፈው ደብዳቤ የሚያመለክተው የመንገድ ላይ ቅስቀሳን በተመለከተ በተመሳሳይ መልኩ በግልፅ ክልከላን የጣለ ሳይሆን በነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ሕገወጥ ቅስቀሳዎች በተደጋጋሚ በመደረጋቸው አደጋ እንዳይደርስ በማሰብ ቢሆንም ቦርዱ አግባብነት አለው ብሎ አያምንም፡፡

ይህ ሁኔታ በወቅቱ በወረዳው የመድረክ ተወካዮች አማካይነት ለኦሮሚያ ክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሪፖርት ደርሶ የምርጫ ክልሉ ኃላፊ በአስቸኳይ ይህንኑ ደብዳቤ ተፈፃሚ እንዳያደርግ ትዕዛዝ የተላለፈና እርምት የተደረገ መሆኑን ቦርዱ አረጋግጧል፡፡

በሁለቱም አባሪዎች የተጠቀሱትን ደብዳቤዎች የፃፉትን የምርጫ ክልል ኃላፊዎች ኃላፊነታቸውን ለአግባብ በመጠቀማቸው ቦርዱ በምርጫ አስፈፃሚዎች የሥነምግባር ደንብ መሠረት ጠርቶ ተገቢውን እርምጃ የሚወስድ መሆኑን ለማስገንዘብ እንወዳለን፡፡

ሁለቱም አባሪዎች በሁለት የምርጫ ክልሎች የተከሰተን ጉዳይ በየራሳቸው የሚያስረዱ ሲሆን በወቅቱ በአንደኛው ምርጫ ክልል ለተፃፈው ለአንደኛው ደብዳቤ ወዲያውኑ ማስተካከያ የተሰጠበት እና በሁለተኛው ደብዳቤ ለተፃፈው ወዲያውኑ በቃል ማስተካከያ እንዲደረግ በክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ትዕዛዝ የተላለፈበት ሆኖ ሳለ፤ በእናንተ በኩል ለማቅረብ የተሞከረው ጉዳዩ በአጠቃላይ በመላ ሀገሪቱ የተካሄደ አድርጎ አጠቃሎ ማቅረብ በመሆኑ አግባብነት የለውም፡፡

በመሆኑም በተሻሻለው የምርጫ ሕግ አዋጅ 532/1999 ዓ.ም. አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 10 መሠረት ቦርዱ ድጋሚ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችል በቂ ምክንያት ሆኖ ባለማግኘቱ አልተቀበለውም፡፡

**በተራ ቁጥር 4.** በአዲስ አበባና አካባቢው በአንዳንድ ቦታዎች ካልሆነ በስተቀር በመላው ሀገሪቱ የመድረክ የምርጫ ምልክቶች፣ ፖስተሮችና የዕጩዎች ፎቶግራፎች እየተቀደዱ መራጩ የመድረክን አላማና የምርጫ ምልክት ለይቶ የራሱን ውሣኔ እንዳይሰጥ ሥልታዊ ማዕቀብ የተጣለበት ሁኔታ ነበር ብላችኋል፡፡

በመሠረቱ ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ፖስተር መቀደድ ጉዳይ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የገዥውን ፓርቲ ጨምሮ የሁሉም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ፖስተሮች መቀደዳቸው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጭምር ጉዳዩ ተነስቶ ከፍተኛ ውይይት ተካሂዶበታል፡፡

በዚህም ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ድርጊቱን በጋራ ያወገዙት ከመሆኑም በላይ ድርጊቱን በፈፀሙ ግለሰቦች ላይ በመንግስት በኩል ተገቢው ክትትል እየተደረገ ህጋዊ እርምጃ የተወሰደ መሆኑ በይፋ ተገልጿል፡፡

ከዚህም በላይ ደግሞ የተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ፖስተር ማጥፋት፣ መቅደድ በሕግ የሚያስቀጣ መሆኑንና የሚመለከታቸው የሕግ አስከባሪ አካላት ድርጊቱን የሚፈፅሙትን ለሕግ በማቅረብ ሕጋዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ በመገናኛ ብዙሃን በተደጋጋሚ በስፋት ለሕዝቡ ትምሕርት ሰጥቷል፡፡

ይህ ሁኔታ ሁሉንም የፖለቲካ ፓርቲዎች የነካ ሆኖ እያለና ድርጊቱ በህገወጥ ግለሰቦች ተፈፅሞ ሲገኝ እርምጃ እየተወሰደ ባለበት እንዲሁም አንድ ፓርቲ ሌላውን ለመጉዳት ያደረገው ለመሆኑ ተጨባጭ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ 85 በመቶ የሆነው መራጭ አርሶ አደር የመድረክን ዓላማና የምርጫ ምልክት ለይቶ የራሱን ውሳኔ እንዳይሰጥ ስልታዊ ማዕቀብ ስለመደረጉ ያቀረባችሁት ማስረጃ እንደማያስረዳ ቦርዱ አረጋግጧል፡፡

**በተራ ቁጥር 5.** መድረክ የስብሰባ አዳራሾችና ሜዳዎችን ተከልክሏል፣ የጠራቸው ስብሰባዎች በገዢው ፓርቲ አባላት ተበትነዋል፣ የቅስቀሳ መሣሪያዎች ተነጥቀዋልና ወዘተ በማለት ላቀረባችሁት አቤቱታ ያስረዳል ብላችሁ ያቀረባችሁትን ማስረጃ ቦርዱ በጥሞና ተመልክቶታል፡፡

በዚህም የቀረበው ማብራሪያ እንጂ ጉዳዩ ስለመፈፀሙ ሊያስረዳ የሚችል ማስረጃ አለመሆኑንና ይልቁኑ አባሪው አንድ ቁንፅል ቦታ ላይ ተፈፀመ ያላችሁትን ጉዳይ ለማሳየት የሞከራችሁበት መሆኑን አረጋግጧል፡፡

**በተራ ቁጥር 6.** የህገ መንግሥቱን አንቀፅ 54 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ መንፈስ በጣሰ ሁኔታ የውክልና ጊዜያቸውን ያላጠናቀቁ የአካባቢ ምክር ቤት አባላት ሲወዳደሩ ቦርዱ በቸልታ በማለፍ የተካሄደ ምርጫ ነው በማለት አቤቱት አቅርባችኋል፡፡

በመሠረቱ የተጠቀሰው የህገ መንግሥቱ አንቀፅ 54 ንዑስ አንቀጽ 1 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ ሁሉ አቀፍ፣ ነፃ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምፅ በሚስጢር በሚሰጥበት ሥርዓት በየአምስት አመቱ በህዝብ የሚመረጡ መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡

በእናንተ በኩል እንደቀረበው የአንድ ምክር ቤት አባል ሆኖ የሚያገለግል ሰው ለሌላ ምክር ቤት አባልነት በምርጫ ሊወዳደር እንደማይችል አልደነገገም፡፡

በዚህ ረገድ የሁሉም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲ ዕጩዎች በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በምርጫ የተቋቋመ የምክር አባላት ሆነው ለቀጣዩ ምክር ቤት ፓርቲያቸው እንዲወዳደሩ ባቀረባቸው ምርጫ ክልል ተመዝግበው የሚወዳደሩ መሆናቸው በግልፅ ይታወቃል፡፡

በዚህም በምርጫው አሸናፊ የሆኑት ፓርቲው ላወዳደራቸው ምክር ቤት በቀጣዩ የምክር ቤት ዘመን ለአንዱ ምክር ቤት ብቻ በአባልነት እንደሚቀጥሉ እና በአንድ ጊዜ ለሁለት ምክር ቤት አባል መሆን እንደማይችሉ የተረጋገጠ ነው፡፡ ህገ መንግሥቱም የደነገገው ይህንኑ ነው፡፡

ቦርዱ ዕጩዎችን ሲመዘገብ በምርጫ ህጉ በግልፅ በተደነገጉት ለዕጩነት የሚያበቁ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ መስፈርት ውጪ ሌሎች በህግ ያልተደነገጉ መስፈርቶችን እናንተ ባቀረባችሁት አቤቱታ መልኩ መጠቀም የሚችልበት የህግ ድንጋጌም ሆነ አሠራር የለም፡፡

በመሆኑም የዕጩዎች ምዝገባ የተካሄደው በህጉ መሠረት ስለሆነ ያቀረባችሁት አቤቱታ ምንም አይነት የህግ መሠረት የሌለው መሆኑን ቦርዱ ያረጋገጠ በመሆኑ አቤቱታችሁን አልተቀበለውም፡፡

**በተራ ቁጥር 7.** በመሠረቱ ላቀረባችሁት አቤቱታ መራጩ ህዝብ ላይ የስነ ልቦና ሽብር በተፈጠረበት ሁኔታ የተካሄደ ምርጫ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

ሰነዱ የገኘው ፓርቲ ሰነድ ለመሆኑ በማህተምም ሆነ በሌላ መልኩ ተረጋግጦ የቀረበ አለመሆኑንን ቦርዱ ለመገንዘብ ችሏል፡፡

ይህም ቢሆን ቦርዱ ካቀረባችሁት ጽሑፍ ይዘት ለመረዳት እንደቻለው የአንድ የፖለቲካ ድርጅት አቋም የተንፀባረቀበት እንጂ በመራጩ ሕዝብ ላይ ሽብር ለመንዛትም ሆነ ለመፍጠር የሚችል ጽሑፍ ሆኖ ስላላገኘው የቀረበውን አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡

**በተራ ቁጥር 8.** ኢህአዴግ የመራጩን ነፃነት በመግፈፍ አንድ ለአምስት ተጠርናፊ የሚል ስልት ተጠቅሞ ህዝቡን አሰፈራርቶ በማስፈረም እና በአገር ሽማግሌዎች በማስወገዝ ድምፅ እንዲሰጥ ተፅዕኖ ባሳደረበት ሁኔታ የተከናወነ ምርጫ ነው ብላችሁ አቤቱታ አቅርባችኋል፡፡

ማስረጃችን ነው ብላችሁ ያቀረባችሁትም የመራጩን ሕዝብ የመምረጥ ነፃነት የሚጋፋ መሆኑን በምንም መልኩ የሚያስረዳ አይደለም፡፡

ይሁን እንጂ ማንኛውም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅት መድረክን ጨምሮ አባላቱንና ደጋፊዎቹን ለራሴ ይጠቅመኛል ባለው መንገድ ሁሉ ለማደራጀት የሚከለክለው ሕግም ሆነ አሠራር የለም፡፡

በተጨማሪም በሽማግሌ ውግዘት ተፈፅሞ ድምፅ ለአንድ ፓርቲ እንዲሰጥ ተፅዕኖ የተደረገ ለመሆኑ ያቀረባችሁት ማስረጃ እንደማያስረዳ ቦርዱ አረጋግጧል፡፡

በዚህ ረገድ ምርጫው በህጉ መሠረት ሚስጢራዊነቱን በጠበቀ መልኩ የተከናወነ መሆኑን ቦርዱ በተጨባጭ አረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ያቀረባችሁትን አቤቱታ ቦርዱ አልተቀበለውም፡፡

**በተራ ቁጥር 9.** አርሶ አደሩን ኢህአዴግን ካልመረጥክ የእርዳታ እህል አታገኝም በሚል የእርዳታ እህል ለገዢው ፓርቲ የምርጫ ቅስቀሳ እና የፖለቲካ መግሪያነት በተጠቀሙበት ሁኔታ የተካሄደ ምርጫ ነው ብላችሁ አቤቱታ አቅርባችኋል፡፡

ያቀረባችሁት ማስረጃ የእርዳታ እህል ለቅስቀሳ ተግባር መዋሉን የሚያረጋግጥ ሆኖ ስላላገኘው ቦርዱ አልተቀበለውም፡፡

**በተራ ቁጥር 10.** ከምርጫው አስቀድሞ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች በህዝቡ ውስጥ በብዛት ተሰራጭተዋል፣ ለአንድ መራጭ ከአንድ የመራጭ ካርድ በላይ ታድሏል፣ ለኢ.ህአዴግ ድምፅ አይሰጡም ተብለው በሚጠረጠሩት ላይ የኢ.ህአዴግ ካድሬዎች ካርዶችን ከምርጫው ዕለት በፊት ሰብስበው ድምፅ እንዳይሰጡ አድርገዋል፣ አንድ መራጭ ከአንድ ጊዜ በላይ ድምፅ እንዲሰጥ ተደርጓል፣ አስቀድሞ የኢ.ህአዴግ የምርጫ ምልክት በተደረገባቸው የምርጫ ወረቀቶች የተሞሉባቸው እና የተቀደዱ ኮሮጆዎች የተገኙበት ነው፣ ኢ.ህአዴግ አንድ ለአምስት ያደራጃቸው መራጮች ወደ ድምፅ መስጫ ክፍል በማስገባት በካድሬዎች መመሪያ ንብ ላይ ምልክት በማሳረፍ የምርጫ ሚስጢራዊነት እና የዜጎች የመምረጥ ነፃነት መብት በተገፈፈበት ሁኔታ የተካሄደ ምርጫ ከመሆኑም በላይ ቦርዱ ለዚህ ሁሉ ሁኔታ ምቹ መንገድ ያመቻቸበት ነው ብላችሁ አቤቱታችሁን አቅርባችኋል፡፡

በመሠረቱ የመራጮች ምዝገባ በህጉ መሠረት ሁሉም የተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች፣ የህዝብ ታዛቢዎች እና የምርጫ አስፈፃሚዎች በተገኙበት ግልፅ በሆነ አሰራር በአግባቡ የተከናወነ ነው፡፡

በመሆኑም በሕጉ መሠረት የመራጮች መዝገብ ከየካቲት 16 እስከ 20 ቀን 2002 ዓ.ም. ድረስ በመላው ሀገሪቱ በሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች ለአምስት ተከታታይ ቀናት ለሕዝብ ይፋ ሆኖ እንዲታይ እና ቅሬታም ካለ እንዲስተናገድ ተደርጓል፡፡

ለአንድ መራጭ ከአንድ ጊዜ በላይ የመራጭነት ካርድ ተሰጥቷል ያላችሁት ተፈፅሞ ከሆነ በወቅቱ አግባብ ላለው የምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሊቀርብና ተገቢውን ውሣኔ ማግኘት የሚገባው እንጂ በዚህ ወቅት ለቦርዱ መቅረብ የሚገባው እንዳልሆነ ቦርዱ አረጋግጧል፡፡

ከአንድ በላይ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ወስደው የተገኙ በጣት የሚቆጠሩ ግለሰቦችም ጉዳይ ቢሆን በወቅቱ አቤቱታው ቀርቦ በሕግ ተገቢውን ቅጣት ያገኙ መሆኑ በእናንተም ጭምር በይፋ የሚታወቅ ነው፡፡

መድረክ ይህንን ህገ ወጥ ነው ያለውን ድርጊት ለህግ ማቅረብና ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኝ ማድረግ ሲገባው ሽፍኖ ለክስ ማዳበሪያ ማድረግ ከምርጫ ስነምግባር ህጉ ያፈነገጠ አካሄድ ነው፡፡

ያም ሆኖ ተመሳሳይ ናቸው ብላችሁ ያቀረባችኋቸው የመራጮች ካርዶችም ቢሆኑ ይዘታቸው ሲታይ በስም ተመሳሳይነት የሌላቸው እና ዋናው ካርድ ቀርቦ ከፎቶ ኮፒው ጋር ያልተመሳከረና ያልተረጋገጠ እንዲሁም እንደማስረጃ የማይቆጠር መሆኑን ቦርዱ አረጋግጧል፡፡

ስለሆነም ቦርዱ ክሱ በማስረጃ ያልተደገፈ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በተመሳሳይ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ከድምፅ መስጫው ዕለት በፊት በህዝብ ውስጥ መሰራጨታቸውን፣ ከመራጮች ላይ ካርድ መሰብሰቡን፣ ከአንድ ጊዜ በላይ አንድ መራጭ ድምፅ መስጠቱን፣ የኢ.ህአዴግ ምልክት የተደረገባቸውን ምልክቶች በኮሮጆ ውስጥ መሞላታቸው፣ አምስት ወይም ስድስት መራጮች በአንድ ጊዜ ሚስጢራዊነቱን በሚጥስ መልኩ አንድ የሚስጢር ድምፅ መስጫ ቦታ ውስጥ ገብተው ድምፅ ስለመስጠታቸው የሚያረጋግጥ አንድም ማስረጃ መድረክ አለማቅረቡን ቦርዱ አረጋግጧል፡፡

ከዚህም በላይ ደግሞ ቦርዱ መድረክ ተፈፅሟል ላላቸው ህገ ወጥ ድርጊቶች ተባባሪ ሆኖ መንገድ ስለማመቻቸቱ የሚያስረዳለት አንድም ማስረጃ አለማቅረቡን እና ይልቁንም ቦርዱ በህዝቡም ዘንድ ሆነ በሀገር ውስጥ እና በዓለም አቀፍ ታዛቢዎች አመኔታንና አድናቆትን ያተረፈ አሰራር ተግባራዊ ማድረጉ የተረጋገጠ መሆኑን ያምናል፡፡

ስለሆነም በተራ ቁጥር 10 የቀረቡት አቤቱታዎች አንድም ማስረጃ ያልቀረበባቸው ከመሆናቸውም ባሻገር፣ ከሕብረተሰቡ፣ ከምርጫ አስፈፃሚዎችም ሆነ ከሀገር ውስጥና የውጪ ሀገር ታዛቢዎችም ጭምር እንዲህ አይነት ክስተት ስለመፈጠሩ ቦርዱ የደረሰው ጥቆማ አለመኖሩን አረጋግጧል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ጉዳዮች ተፈፃመዋል በተባለባቸው ቦታዎች በምርጫ ሕጉ በተቀመጠው ሕጋዊ አሠራር መሠረት ስለማቅረባችሁ በአቤቱታችሁ ውስጥም ሆነ ማስረጃ ብላችሁ ባቀረባችኋቸው አባሪዎች የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

በመሆኑም አቤቱታችሁን ቦርዱ ውድቅ አድርጎታል፡፡

**በተራ ቁጥር 11.** መድረክ ከውድድር ወጥቷል የሚል ሀሰተኛ ሰነድ ተበትኖ ምርጫ ቦርድ ባላስተባበለበት ሁኔታ የተካሄደ ምርጫ ነው በሚል አቤቱታ አቅርባችኋል፡፡

መድረክ ከውድድር ወጥቷል የሚለውን ደብዳቤ ያመጣው እራሱ መድረክ ነው፡፡ ይህንን ደብዳቤ ከየት እንዳገኘ የሚያውቀው እራሱ መድረክ ነው፡፡ በደብዳቤው ላይ የተፈረመው ፊርማ እና ማህተም የማን እንደሆነ የሚያውቀው እራሱ መድረክ ነው፡፡

ሀሰተኛ የተባለው መልዕክት ተላለፈ የተባለው ስለ መድረክ ከምርጫ መውጣት ነው፡፡ ይህንኑ ሀሰተኛ መልዕክት በይፋ ወጥቶ ማስተባበል ያለበት በየትኛውም መመዘኛ ኃላፊነቱ የመድረክ እንደሆነ ቦርዱ በፅኑ ያምናል፡፡ ይኸው የቦርዱ አቋም ለመድረኩ ሊቀመንበር በወቅቱ ግንቦት 14 ቀን 2002 ዓ.ም. በግልፅ ተነግሯቸዋል፡፡

ስለሆነም በዚህ ረገድ መድረክ ያቀረበውን አቤቱታ ቦርዱ አልተቀበለውም፡፡

**በተራ ቁጥር 12.** ተቀማጭና ተዘዋዋሪ ወኪሎቻችን ምርጫ አስፈፃሚዎች በፈጠሯቸው ደባዎች መታወቂያ ተከልክለዋል፣ ያልተፈረሙ መታወቂያዎች ተሰጥተዋል እና ወደ ድምፅ መስጫ ጣቢያ እንዳይገቡ በታጣቂዎች በተፈፀመው ክልከላ ምክንያት ምርጫው ከሃምሳ በመቶ በበለጠ ደረጃ ተወካዮቻችን ባልተገኙበት ሁኔታ የተካሄደ ነው በማለት አቤቱታ አቅርባችኋል፡፡

በህጉ መሠረት ፓርቲዎች ተቀማጭ እና ተንቀሳቃሽ ወኪሎቻቸውን ከምርጫ ዕለት አሥር ቀን በፊት ለየምርጫ ክልሉ ዝርዝሩን ማቅረብ እንደሚኖርባቸው የሚደነግግ ቢሆንም ይህንኑ ተግባራዊ የሚያደርግ የጊዜ ሠሌዳ ገና በዓመቱ ጅምር ላይ /ኅዳር 2002 ዓ.ም./ ቦርዱ በራሱ ወጪ አሳትሞ ለሁሉም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች መድረክን ጨምሮ ማሠራጨቱ የታወቀ ቢሆንም፣ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጣችሁ በጠየቃችሁት መሠረት ምርጫ ሁለት ቀን እስኪቀረው ድረስ ወኪሎቻችሁን እንድታቀርቡ ቦርዱ የቅርብ ክትትል በማድረግ የተፈፀመ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

በወኪሎቻችን ላይ ተፈፅሟል ያላችሁትን በደል በወቅቱ በህጉ መሠረት በየደረጃው በሚገኙ የምርጫ ጽሕፈት ቤቶች ስለማቅረባችሁ እና የተሰጣችሁን ውሳኔ በሚመለከት አያይዛችሁ ያቀረባችሁት ማስረጃ እንደሌለ ቦርዱ ተገንዝቧል፡፡

ይህ ደግሞ ወኪሎቻችሁን በራሳችሁ ምክንያት ማቅረብ ባልቻላችሁባቸው ቦታዎች ሁሉ አለአግባብ እንደተከለከላችሁ በማስመሰል ያቀረባችሁት እንደሆነ እና ይህንኑ በአጠቃላይ ከ50 በመቶ በላይ በሚሆኑት ቦታዎች ላይ አለወኪሎቻችን ምርጫ ተካሂዷል የሚለውን በማስረጃ ያልተደገፈ አቤቱታችሁን ለማጠናከር ያቀረባችሁ መሆኑን ቦርዱ ተረድቷል፡፡

የአውሮፓ ህብረት ታዛቢ ቡድን ሪፖርትም ቢሆን በጥቂት ምርጫ ጣቢያዎች ላይ ማለትም ከ44 ሺህ የምርጫ ጣቢያዎች 800 በሚሆኑት ላይ ብቻ ተመስርቶ የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ወኪሎች መገኘታቸውን ከማረጋገጥ ይልቅ በመድረክ ወኪሎች ላይ ለይቶ ግልፅ ባልሆነ መልኩ ያነጣጠረ መደምደሚያ ላይ የደረሰበትን ቁንፅል ጉዳይ ለአቤቱታችሁ ማጠናከሪያ ማቅረባችሁ ፍፁም አግባብነት እንደሌለው ቦርዱ ተገንዝቧል፡፡

በመሆኑም ይህንኑ አቤቱታ ቦርዱ አልተቀበለውም፡፡

**በተራ ቁጥር** 13. ወኪሎቻችን ህገወጥ ድርጊት በመቃወማቸው ምክንያት ከየምርጫ ጣቢያዎቹ እየተደበደቡ ተባረዋል፣ ታስረዋል፣ ህግና ሥርዓቱ ሊከበር ባለመቻሉ ለቀው እንዲወጡ በተገደዱበት ሁኔታ የተካሄደ ምርጫ ነው ብላችኋል፡፡

ለዚህም ያስረዳልናል ብላችሁ ያቀረባችሁት አባሪ ቁጥር 10 ሲሆን ማስረጃ ብላችሁ ያቀረባችሁት ከአቤቱታው ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው መሆኑን ቦርዱ አረጋግጧል፡፡

አባሪ ቁጥር 10 ቀደም ሲል ከምርጫ ዕለት በፊት ገና ለገና ሊፈፀም ይችላል ብላችሁ ያቀረባችሁት ያልተረጋገጠ ሥጋት እንጂ በምርጫ ቀን ተፈፀመ ስላላችሁት የወኪሎች መባረር ሊያረጋግጥ የሚችል አለመሆኑን ቦርዱ ተረድቷል፡፡

በመሆኑም ቦርዱ አቤቱታችሁን አልተቀበለውም፡፡

**በተራ ቁጥር** 14፣ 15 እና 16.

በድምፅ መስጫው ዕለት ተፈፀሙ ስላላችኋቸው ግድፈቶች በዝርዝር አቅርባችኋል፡፡

ቦርዱ ያቀረባችሁትን አቤቱታ ሲመረምር ተፈፀሙ የተባሉትን ግድፈቶች ሊያስረዳ የሚችል አንድም ማስረጃ አለማቅረባችሁን ተገንዝቧል፡፡

ይልቁንም በድምፅ መስጫው እለት በመላው ሀገሪቱ መራጩ ህዝብ በተረጋጋ ሁኔታ ድምፁን ሲሰጥ የዋለበት፣ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት በህጉ መሠረት በየምርጫ ጣቢያው የህዝብ ታዛቢዎች፣ የፓርቲ ወኪሎች እና የምርጫ አስፈፃሚዎች እንዲሁም የሀገር ውስጥ እና የአለም አቀፍ ታዛቢዎች በተገኙበት የተጀመረ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

ስለሆነም ቦርዱ ያቀረባችሁትን አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡

ምርጫው ነፃ፣ ፍትሐዊና ዲሞክራሲያዊ ሆኖ እያለ ቦርዱ በሐቅ ሁላችሁንም በአንድ ዐይን እያገለገለ መሆኑን እያወቃችሁ መድረኩ ምንም ፍትሐዊ አገልግሎት እንዳላገኘ በመቁጠር ምርጫው ይደገም ለሚለው ጥቅል ክስ እንደምክንያት ማቅረቡ ቦርዱን በእጅጉ አሳዝኖታል፡፡

በ24/09/2002 በቁጥር መድረክ/304/2002 ለቦርዱ ጽሕፈት ቤት ባቀረባችሁት አቤቱታ በአጠቃላይ ምርጫው ፍትሃዊ እና ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ እና ህገወጥነት የሰፈነበት ስለመሆኑ ቀደም ሲል ታቀርቡት የነበረውን አቤቱታ እንደማስረጃ ማቅረባችሁ በቦርዱ በኩል ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም ባቀረባችሁት አቤቱታ መሠረት ድጋሚ ምርጫ ለማካሄድ ምንም ማስረጃ እና የህግ መሠረት የሌለው መሆኑን ቦርዱ አረጋግጦ ጥያቄያችሁን ውድቅ አድርጎታል፡፡

ከሠላምታ ጋር

<u>እንዲያውቁት፣</u>

- ለክቡር ፕሮፌሰር መርጋ በቃና

የቦርዱ ሰብሳቢ

<u>አዲስ አበባ፣</u>